# በኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት
# የኢንፎርሜሽንና ኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት
## የሚዘጋጅ ወርሃዊ ዲጂታል መጽሔት

**መስከረም /2018**







**እንኳን ደስ አላችሁ !**



## ማውጫ


የንግዱ ማኅበረሰብ ሽልማት——-————————-—1

AfCFTA ግብይት ስራ መጀመር ——————————1

ፕሬዚዳንቱ ስለ AfCFTA ግብይት —————————-2

የምክር ቤቱ ሽልማት———————————————-3

ፕሬዚዳንቱ ስለ ሽልማቱ ያስተላለፉት————3

AfCFTA ግብይት ፓናል ውይይት—————————-4

አቶ ሰብስብ በኢቢኤስ ቲቪ ያደረጉት ቆይታ———5

ከጅቡቲ ምክር ቤት ጋር ውይይት——————-6

2ኛው የኢትዮ ጂቡቲ የቢዝነስ ጉባዔ ——————-7

ዋና ጸሐፊው ከዓለም ባንክ ጋር ውይይት—-8

ዋና ጸሐፊው CIPE EHIOPIA ጋር ውይይት———-8

ከማሌዥያ ኤምባሲ ልዑክ ጋር ውይይት————9

ለሴቶች ስልጠና መጀመር———————————10

ለሴቶች ስልጠና መጠናቀቅና ሰርተፊኬት————10

በማዕከላዊ ን/ም/ቤት ኢትዮጵያ ስልጠና ———11

የቢዝነስ አሰልጣኞች ስልጠና—————————12

አድራሻ——-—————————————————14


## እንኳን ደስ አላችሁ !







**የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚደንት ሰብስብ አባፊራ አባጆቢር በ7ኛው የታማኝ ግብር ከፋዮች ከክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) የእውቅና እና ሽልማት ለተቀበሉ የንግዱ ማኅበረሰብ አባላት የእንኳን ደስ አላችሁ መልዕክት አስተላለፉ።**

ፕሬዚደንቱ አክለውም የንግዱ ማህበረሰብ በሰበሰበው ሀብት ብዛት ሳይሆን በአገራዊ አስተዋፅኦ መወዳደር አለባቸው ብለዋል ::

በተለይ የሚጠበቅባቸውን ግብር በመክፈል፤ በምርትና አገልግሎት ጥራት እንዲሁም በማህበራዊ ግልጋሎት የዉድድር ሜዳዎች አንፃር ጠንክሮ መስራት እንደሚገባም ገልፀዋል።

..........................................................

Kaffaltoota gibiraa amanamoo ta'an 700 ta'aniif beekamtii fi badhaasni kennameera. Hundi keessan baga gammaddan.

Hawaasni daldalaa hanga qabeenya walitti qabuun osoo hin taane, gumaacha biyyaalessaa isaaniitiin beekamtii argachuu qabu. Keessattuu gibira guddaa kaffaluun, qulqullinni oomishaa fi tajaajilaa fi tajaajilli hawaasummaa ulasgaalee dorgommii ta'uu qabu. Guyyaa har'aas daldaltoota 700 ta'aniif mallattoo jaalala biyyaa kan ta'e Obbo Yadeta Junaid dabalatee badhaasa PLATINUM fi badhaasa adda addaa Ministira Muummee Dr. Abiy Ahimadiin badhaafamaniiru.

## በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የአፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጣና (AfCFTA) ግብይት የማሥጀመሪያ መርኃ-ግብር ተካሄደ ፡፡






በማስጀመሪያ መርሐ ግብሩ በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ማዕረግ የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ማስተባበሪያ ማዕከል ኃላፊ እና የብልጽግና ፓርቲ ም/ፕሬዚዳንት አደም ፋራህ፣ የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስትር አለሙ ስሜ (ዶ/ር)፣ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ካሳሁን ጎፌ (ዶ/ር)፣ የአፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጣና ዋና ጸሐፊ ዋምኬሌ ሜኔ ተወካይ፣ የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚደንት አቶ ሰብስብ አባፊራ አባጆብርና ሌሎች ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎችና የንግዱ ማኅበረሠብ ተወካዮች ተገኝተዋል።





ግብይቱ ሲጀመር ሥጋ፣ አትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም ቡና፣ የጥራጥሬ ምርቶችና የቅባት እህሎች በኢትዮጵያ አየር መንገድ ካርጎና በየብስ ትራንስፖርት ወደ ኬንያ፣ ሶማሊያ እና ደቡብ አፍሪካ ተልከዋል። ኢትዮጵያ በአፍሪካ አህጉራዊ ነጻ የንግድ ቀጣና ስምምነት ተግባራዊነት ከአፍሪካ ህብረት ምስረታ ጀምሮ በግንባር ቀደምነት ስትሠራበት የቆየችው ጉዳይ መሆኑ ይታወቃል።ሥምምነቱ ለአባል ሀገራቱ የኢኮኖሚ ለውጥ እንዲሁም እድገትና ለውጥ፣ ለገበያ መስፋፋት፣ ህዝቦችን በንግድ የሚያሥተሣሥር እንዲሁም ኢንቨሥትመንት የሚያበረታታ የወጭና ገቢ ንግድን የሚያዘምንና የተሣለጠ የንግድ ሥርዓት መፍጠር የሚያሥችል ነው።

**በአፍሪካ አህጉራዊ ነጻ ንግድ ቀጣና ስምምነት ማዕቀፍ ግብይት መጀመሩ በአለም አቀፍ የንግድ ትስስር የሚገባንን ቦታ እንድንይዝ አስቻይ ሁኔታ የሚፈጥርልን ይሆናል ሲሉ የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ሰብስብ አባፊራ አባጆቢር ገለፁ።**





በአፍሪካ አህጉራዊ ነጻ ንግድ ቀጣና ስምምነት ማዕቀፍ ታሪካዊውን የግብይት ማስጀመሪያ መርኃ-ግብርን በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ማዕረግ የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ማስተባበሪያ ማዕከል ዋና ኃላፊ እና የብልፅግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንት ክቡር አቶ አደም ፋራህ፣ ሚኒስትሮችና ክቡራን እንግዶች በተገኙበት በስመ ጥሩና የሃገራችን የክብር ምልክት በሆነው የኢትዮጵያ አየር መንገድ የመጀመሪያውን ጭነት ተጀምሯል ።

ከኢትዮጵያ አየር መንገድ ካርጎ በተጨማሪ በየብስ ትራንስፖርትም የማስጀመሪያ ጭነት ሽኝትን አከናውነናል። በዚህም መሰረት በዛሬው ዕለት ወደ ጎረቤት ሃገራት ኬንያ የበቆሎ ምርት፣ ሶማሊያ የአንስት ስጋ፣ እንዲሁም ወደ ደቡብ አፍሪካ በሎቄ የላክን ሲሆን 1.3 ቢሊዮን የህዝብ ብዛትና ሰፊ የገበያ ዕድል ላላት አህጉራችን አፍሪካ የንግድ ትስስርን ለማሳለጥ ዝግጁ ስለመሆናችን ተምሳሌታዊ ማሳያ ነው ብለዋል ፕሬዚዳንቱ።

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር አስተባባሪነት የተተገበረው ይህ አህጉራዊ ነጻ ንግድ ቀጣና ስምምነት የአፍሪካ ህብረት መስራች አባል እና ለፓን አፍሪካኒዝም ግንባር ቀደም ተሟጋች ለሆነችው ኢትዮጵያ ትልቅ ምዕራፍ ነው። በአለም አቀፍ የንግድ ትስስር የሚገባንን በታ እንድንይዝም አስቻይ ሁኔታ የሚፈጥርልን ይሆናል።

Guyyaa har'aa, waliigaltee Naannawaa Daldala Walabaa Ardii Afrikaa jalatti, sagantaa jalqabsiisa daldala jalqabaa bakka Sadarkaa Itti Aanaa Ministira Muummeetti Hoogganaa Wiirtuu Qindeessaa Ijaarsa Sirna Dimokiraasiifi Itti Aanaa Pireezidaantii Paartii Badhaadhinaa Kabajamoo Obbo Adem Faraah, Ministeerotaa fi keessummoonni biroon argamanitti mallattoo ol ka'insa biyya keenyaa kan ta'e Daandii Qilleensaa Itoophiyaatti eegalchiifneerra. Fe'umsa kaargoo Daandii Qilleensaan alattis geejjiba lafarraatiin fe'umsa jalqabaa ergineerra. Jalqabsiisa har'aatiin, oomishaalee keenya biyyoota ollaa Keeniyaatti Boqolloo,

fi Somaaliyaatti Foon loonii, akkasumas gara Afrikaa Kibbaatti boloqqee ergineerra. Kanaanis Ardii Afriikaa baay'ina uummataa biliyoona 1.3 fi carraa gabaa bal'aa qabduuf hariiroo daldalaa cimaa uumuudhaaf kutannoon socho'uu keenya kan agarsiisudha. Waliigaltee Naannoo Daldala Walabaa Ardii Afrikaa qindeessummaa Ministeera Daldalaafi Walitti-hidhamiinsa Naannawaatiin hojiirra oole kun, biyya keenya Itoophiyaa seenessa Pan-Afriikaanisim adda durummaan hooggantuuf boqonnaa guddaadha.

**The President of the Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations, Sebsibe Abafira Abajobir, stated that Ethiopia's commencement of trade under the framework of the African Continental Free Trade Area (AfCFTA) will create a favorable condition for the country to secure a significant place in global trade relations.**

**On this day, the historic launching ceremony for Ethiopia's first trade under the AfCFTA framework was held, in the presence of His Excellency Ato Adem Farah, Deputy Prime Minister, Coordinator of Democratic System Building at the Prime Minister's Office, and Deputy President of the Prosperity Party.Several ministers and high-ranking officials also attended the event.**






## የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት በአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጣና ስምምነት ትግበራ ባደረገው አስተዋጽዖ እውቅናና ሽልማት ተበረከተለት ::



የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት በአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጣና ስምምነት ትግበራ ባደረገው አስተዋጽዖ እውቅናና ሽልማት ተበረከተለት ::

የተሰጠውን የእውቅና ሽልማትም የምክር ቤቱ ፕሬዚዳንት ሰብሰብ አባፊራ አባጆቢር በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ማዕረግ የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ማስተባበሪያ ማዕከል ኃላፊ እና የብልጽግና ፓርቲ ም/ፕሬዚዳንት ከአቶ አደም ፋራህ እጅ ተቀብለዋል::





የአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጣና ስምምነት ትግበራ የላቀ አስተዋፅኦ ላበረከቱ ሌሎች አካላትም እውቅናና ሽልማት ተበረክቶላቸዋል።

**የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት በአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጣና ስምምነት ትግበራ ባደረገው አስተዋጽዖ እውቅናና ሽልማት በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ማዕረግ የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ማስተባበሪያ ማዕከል ኃላፊ እና የብልጽግና ፓርቲ ም/ፕሬዚዳንት ከአቶ አደም ፋራህ እጅ ተቀብያለው ::**



የአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጣና ስምምነት ትግበራ የላቀ አስተዋፅኦ ላበረከቱ ሌሎች አካላትም እውቅናና ሽልማት ተበረክቶላቸዋል።

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ሰብስብ አባፊራ አባጆቢር ...................................................................

Har’a Manni Maree Daldalaa fi Industirii Itiyoophiyaa hojiirra oolmaa Waliigaltee Daldala Walaba Afrikaa (AfCFTA) keessatti gumaacha godheef itti aanaa muummicha ministeeraa, Hogganaa Giddugala Qindeessaa Paartii Dimokiraasii fi Badhaadhinaa (PCDP) fi Pireezidaantii Itti Aanaa Paartii Badhaadhinaa Atoo Adem Farah irraa badhaasa fi beekamtii argateera.

Qaamoleen biroo raawwii Waliigaltee Daldala Walaba Afrikaa (AfCFTA) keessatti gumaacha olaanaa taasisanis beekamtiin kennameefii badhaafamaniiru.

# የአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጣና ስምምነት ትግበራ በተመለከተ የፓናል ውይይት ተካሄደ ።

**የአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጣና ስምምነት ትግበራ በተመለከተ የፓናል ውይይት እየተካሄደ ነው።**




የፓናል ውይይቱ በተለይም ሀገሪቱ ከምትተገብረው የኢኮኖሚ ሪፎርም አንፃርና በመንግስትና በግሉ ዘርፍ መካከል ባለው ግንኙነት ዙሪያ ያተኮረ ነው0።

በውይይቱ በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ማዕረግ የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ማስተባበሪያ ማዕከል ኃላፊ እና የብልጽግና ፓርቲ ም/ፕሬዚዳንት አደም ፋራህ፣ የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስትር አለሙ ስሜ (ዶ/ር)፣ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ካሳሁን ጎፌ (ዶ/ር)፣ የአፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጣና ዋና ጸሐፊ ዋምኬሌ ሜኔ ተወካይ፣ የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚደንት አቶ ሰብስብ አባፊራ አባጆብርና ሌሎች ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎችና የንግዱ ማኅበረሠብ ተወካዮች ተገኝተዋል፡፡



የንግድና ቀጣናዊ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ወ/ሮ ያስሚን ወሀብረቢ በአወያይነት በተሠየሙበት የፓናል ውይይት የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፉ ማህበራት ም/ቤት ዋና ፀሐፊ ዶክተር ቀነኒሳ ለሚ



(ተባባሪ ፕሮፌሰር)ን ጨምሮ የመንግስትና የግሉ ዘርፍ ተወካዮች በፓናሊስትነት ተሣትፈዋል።
ዶክተር ቀነኒሳ ለሚ (ተባባሪ ፕሮፌሠር) ምክር ቤቱ ከትግበራውና የግሉ ዘርፍ

ሚና ጋር በተያያዘ በስምምንቱ ዙሪያ የላቀ ግንዛቤ እንዲኖር ለማድረግ የስልጠናና የአቅም ግንባታ ስራዎች በስፋት ሲሰራ እንደነበርና ወደፊትም

ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አብራርተዋል

## የኢትዮጵያ ንግድ እና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ክቡር አቶ ሰብስብ አባፊራ ከEBS TV ጋር ባደረጉት ቃለመጠይቅ ያነሷቸዉ አንኳር ነጥቦች

=====================



የኢትዮጵያ ንግድ እና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ክቡር አቶ ሰብስብ አባፊራ ከEBS TV ጋር ቃለመጠይቅ አድርገዋል። በቃለመጠይቁም ያነሱዋቸዉን አበይት ነጥቦች እንደሚከተለዉ ቀርቧል።
የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ከተመሰረተ 80 ዓመት የሞላዉ መሆኑን እና በሀገራችን የንግድ አገልግሎትን ለማሳለጥ የተቋቋመ አንጋፋ መንግስታዊ ያልሆነ ለትርፍ የማይሰራ የግሉ ዘርፍ ተቋም መሆኑን ገልጸዋል።

1. የኢትዮጵያ ንግድ እና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት አላማዎች እና ተግባራትን በተመለከተ

• ለንግዱ ማህበረሰብ የተለያዩ አገልግሎቶችን መስጠት

•የአባላትን መብትና ጥቅም ማስከበር

• የአገሪቱ ምርቶችና አገልግሎቶች ኢትዮጵያን ጨምሮ በመላው ዓለም እንድታዋወቁ ማድረግ

• በአገሪቱ የንግድና ኢንቨስትመንት ስራዎች እንዲያድጉ (እንድስፋፉ) ማድረግ

• በመንግስትና በንግዱ ማህበረሰብ መካከል እንደ ድልድይ ሆኖ ማገልገል መሆኑን አብራርተዋል።

2. የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ለንግዱ ማህበረሰብ ድምጽ ሆኖ የሚያገለግልና ጥብቅና የሚቆም ተቋም መሆኑን በተመለከተ ክቡር ፕሬዝዳንቱ ያነሱት አበይት ነጥቦች

•የንግድ ምክር ቤቱ ጥብቅና የሚቆመው አንድም በቀጥታ፤ሁለትም በተዘዋዋሪ የሚገለጽ መሆኑን፤

• ለምሳሌም የመንግስት ፖሊሲዎች አዋጆች ከመውጣታቸው በፊት በመንግስት ግብዣ የአዋጁ ረቂቅ ላይ እንድንወያይ የሚደረግ መሆኑን፤ ረቂቁ ላይ የራሳችንን (የም/ቤቱን) ሀሳብ የሚንሰጥ በአዋጁ ዉስጥም ሚዛናዊነቱን ጠብቆ እንዲካተት እንደሚደረግ

• አዋጁ ከወጣ በኋላም (በትግበራ ወቅት) አስኪያጅ ያልሆኑ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ ወይም አዋጁ ችግር አለበት ተብሎ ከታሰበ በተቋሙ እንደሚጠና፤ የጥናት ውጤቱ ለመንግስት እንደሚቀርብ፤ በጥናቱ ላይ መንግስትና ባለድርሻ አካላት እንደዚሁም መንግስትና ባለጉዳዩ የንግዱ ማህበረሰብ ተገናኝቶ እንዲወያይ እንደሚደረግና የተሰጠዉን የመፍትሄ ሀሳብ ስራ ላይ እንዲዉል እንደሚደረግ

3. ከግብር እና ከንግድ ስርዓት ጋር በተገናኘ በተደጋጋሚ የሚወጡ የአሠራር ማሻሻያዎችና አዳዲስ በሚወጡ ህጎች የንግድ ምክር ቤቱ ተሳትፎና ሚናን በተመለከተ

• መንግስት ለግሉ ሴክተር የሰጠዉ ትኩረት መኖሩን፣ ከዛ አንጻር በሚወጡ አዋጆች ላይ የንግድ ም/ቤቱን በሰፊዉ የማሳተፍ ሁኔታዎች መኖሩን፣ ከዛም አልፎ ጫና የሚፈጥሩ አዋጆች የሚወጡበት ሁኔታ ሊኖር ቢችልም መንግስት የንግድ ም/ቤቱን ያላዳመጠበት ጊዜ አለመኖሩን
• ይህም በረቂቅ ህጎች ላይ ቀድሞ በመወያየት አዋጆችና ደምቦች ከተሻሻሉና ከወጡ በኋላም የግሉ ሴክተር ድምጽ ሆነን መንግስትን ከመሞገት ከመወትወትና የአድቮኬሲ ስራዎችን ከመስራታችን የተነሳ እንደዚሁም ከመንግስት ጋር በመነጋገርና በመደማመጥ ህጎች እንዲሻሻሉ የተደረገበት ሁኔታ የም/ቤቱ ድርሻ ሰፊ መሆኑን አንስተዋል።
4. የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት መጠናከርና አቅም መፍጠር ጤናማ የሆነ የተስተካከለ የቢዝነስ ስርዓት እንዲፈጠር ማስቻል ስለሆነ ከዚህ አኳያ ለንግዱ ማህበረሰብና ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ እድገት ስለ ሚኖራቸው አስተዋጽኦ በተመለከተ

• በአለም ላይ የንግድ ምክር ቤት አስፈላጊነት አጠራጣሪ እንዳልሆነ፤ የንግድ ግንኙነት፣ የንግድ ዳኝነት ፣የንግድ ልውውጦች ከየትኛውም ሀገራት ጋር የሚደረገው በንግድ ምክር ቤት በኩል መሆኑን
• ለምሳሌ ብዙ አገራት የምርት አገር ማረጋገጫ የሚሰጡት የንግድ ምክር ቤቶች መሆናቸዉን ገልጸዋል። የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤትም አንዱ ከሚሰጠው አገልግሎት የምርት አገር ማረጋገጫ (Certificate of Origin) የሚሰጥ መሆኑን
• የአድቮኬሲ ስራዎችን የሚሰራ መሆኑን
• ንግድና ኢንቨስትመንት ወደ ሀገራችን እንዲሳብና እንዲስፋፋ የራሱን ሚና የሚጫወት መሆኑን
• ያሉትን የኢንቨስትመንት እድሎችን የሚያስጠናና የተጠኑትን የኢንቨስትመንት እድሎችን ለባለሀብቶች በማቅረብ ለእንቨስትመንት የሚጋብዝ መሆኑን
• የንግዱ ማህበረሰብ ዉጭ ሄዶ በሰላም ገዝተው ሽጦ እንዲመለስ፤ እዚያ እንኳን ችግር ቢያጋጥመው እዚያ ካለው ንግድ ም/ቤት ጋር በመግባባት በመነጋገር እንዲፈታ የማድረግ ስራ በንግድ ምክር ቤታችን በኩል የሚሰራ መሆኑን

5. ንግድ ም/ቤቱ ሀገራዊ ትርጉም ያለው ስራዎችን ለመስራት ራሱን እያበቃ ያለበትን አካሄድ በተመለከተ
• ምክር ቤቶችን ጠንካራ ለማድረግ የመንግስት ፖሊሲ ወሳኝ መሆኑን
• አባላት ምክር ቤታቸውን ተቀብሎ ድርሻቸውንና ሚናቸውን መወጣታቸው አስፈላጊ መሆኑን
• መንግስት ለኢኮኖሚ እንቅስቃሴና ለአገር ግንባታ ማነቆ የሆኑትን ባአጠቃላይ ፖሊሲዎችን ቢቀይርም አሁን ያለዉ የንግድ ም/ቤቱ አዋጅ ለብዙ አመታት የቆየና ኢትዮጵያ የያዘችዉን የልማት እቅድና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ለማስፈጸም እንደማይመጥንና አዋጁን ለማሻሻል ረቂቁ ለመንግስት ተልኮ እየተጠበቀ መሆኑን
• በመሆኑም ለጥንካሬ ማጣቱ መድረስ ያለበት ቦታ ያመድረሱ፣ ሚናዉን በአግባቡ አለመወጣቱ ወቅቱን የዋጀ የሚያሰራ አዋጅ አለመኖሩ ምክኒያት መሆኑን
• ይሁን እንጂ ንግድ ም/ቤቱ አዋጁ ባለመሻሻሉ እጁን አጣጥፎ ያልተቀመጠና ም/ቤቱን አዲስ መዋቅር በመዘርጋት፣ በአዳዲስ የሰዉ ሃይል በመገንባት፣ የገቢ ምንጩን በማሻሻል፣ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በመዘርጋት፣ አባል ለሆኑም ሆነ አባል ላልሆኑ ሁሉ ሳያዳላ ፈጣን አገልግሎት በመስጠት ም/ቤቱ አላማዉን እያሳካ እንደሆነ አብራርተዋል።

6. የንግድ ም/ቤቱ አባላት፣ የአባልነት መስፈርት እና የአባልነት ትሩፋትን በተመለከተ

• የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት 13 የክልል ምክር ቤቶች፣ 6 የዘርፍ ማህበራት፣ 2 የከተማ አስተዳደር አዲስ አበባ እና ድሬዳዋን ጨምሮ ባጠቃላይ 21 የንግድ ምክር ቤቶች በአባልነት እንዳለዉ
• በእነዚህ 21 ምክር ቤቶች ስር ደግሞ የተለያዩ በየከተማው የተደራጁ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ተደራጅተዉ እየሰሩ መሆኑን
• የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት እና በስሩ የሚገኙት አባላት እና መዋቅራቸዉ ለሁሉም የንግዱ ማህበረሰብ የመንግስት የልማት ድርጅቶችን ጨምሮ ሳያዳሉ አገልግሎት እየሰጡ ነው።
7. ተቋሙ የተሻለ ግንዛቤና አረዳድ እንዲፈጠር መሰራት ያለበትን በተመለከተ

-----------------------------------------

• በቂ ግንዛቤ በመፍጠሩ ዙሪያ በስፋት መሰራት ቢኖርበትም፤ የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤትም ሆነ ታች ያሉት ቅርንጫፍ ንግድ ምክር ቤቶቻችን የግሉ ሴክተር ጥላና ከለላ እንዲሁም አንደበታቸዉ መሆናቸዉን መረዳት እንደሚገባ

• የንግዱ ማህበረሰብ የድጋፍ ደብዳቤዎችን፣ የግልግል ዳኝነትን፣ስልጠናዎችን የፈለገ ቀን ብቻ ወደ ም/ቤቱ መምጣት እንደሌለበት

• የንግዱ ማህበረሰብ ተቋሙ የኔ ተቋም ነዉ ብሎ አባል በመሆን በቅርብ አብሮ መስራት እንዳለበት አበይት መልእክቶችን አስተላልፈዋል።

# 2ኛው የኢትዮ ጂቡቲ የቢዝነስ ማስፋፊያ ጉባዔ ተካሄደ::




“የሎጂስቲክስ አቅርቦት ለቀጣናዊ የቢዝነስ ትስስር” በሚል መሪ ሐሳብ ሁለተኛው የኢትዮ ጂቡቲ የቢዝነስ ማስፋፊያ ጉባዔ በጂቡቲ ተካሄደ ።

ጉባዔው የኢትዮጵያ እና ጂቡቲን የሎጂስቲክስ ትብብር ለማሳደግ ያለመ ሲሆን÷ የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማሕበራት ም/ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት አይናለም አባይነህ (ዶ/ር)፣ የጅቡቲ ንግድና ቱሪዝም ሚኒስትር ሞሀመድ ዋርሳማ ዲሬህ እና የዘርፉ ተቋማት ኃላፊዎች ተገኝተዋል።



የኢትዮጵያ ሎጂስቲክስ ዘርፍ ማሕበር ፕሬዚዳንት ኤልሳቤት ጌታሁን ጉባዔው በሎጂስቲክስ ዘርፍ የሚስተዋሉ ችግሮችን በመቅረፍ ቀጣይነት ያለውን የቢዝነስ ዕድገት ለማፋጠን እንደሚረዳ ተናግረዋል።

ጉባዔው ለእድገትና ትራንስፎርሜሽን በሚፈጥረው ዕድል ለቀጣናው ተምሳሌታዊ ትብብር እንደሚሆን ጠቅሰዋል።

የጂቡቲ የንግድና ቱሪዝም ሚኒስትር ሞሀመድ ዋርሳማ ዲሬህ በበኩላቸው÷ ጉባዔው የሁለቱን ሀገራት የንግድ ትብብር በማሳደግ የኢትዮ ጂቡቲ ኮሪደርን ይበልጥ ውጤታማ የሚያደርግ መሆኑን አንስተዋል።



በሁለቱ ሀገራት መካከል የትስስር፣ የዕውቀት ሽግግር እና ስትራቴጂካዊ ትብብር ለመፍጠር የሚያስችል መድረክ እንደሆነም ጠቁመዋል። በመድረኩ የሎጂስቲክስ ዘርፉን አቅም ለማሳደግ መሰል ትብብሮች ያላቸው ሚና ከፍተኛ መሆኑ ተጠቅሷል።

ጉባዔውን የኢትዮ ሎጂስቲክስ ዘርፍ ማሕበር ከኢትዮጵያ ንግድ ምክር ቤት፣ ከጂቡቲ ንግድ ምክር ቤት እና ትሬድ ማርክ አፍሪካ ጋር በመተባበር ማዘጋጀታቸው ተገልጿል።

የቀጣናውን ሀገራት የሎጂስቲክስ ንግድ ትስስር ለማጠናከር ያለመው የመጀመሪያው ዙር መድረክ አዲስ አበባ ተካሂዷል።



**የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ከጅቡቲ ንግድ ምክር ቤት ጋር የሁለቱን አገሮች የንግድ ግንኙነት ማጠናከር ላይ ተወያይቶ በቀጣይ ምን መደረግ እንዳለበት አቅጣጫ አስቀምጧል።**





ዉይይቱ የኢትዮጵያ ሎጂስቲክስ ዘርፍ ማህበራት ከኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት እና ከጅቡቲ ንግድ ምክር ቤት ጋር በጅቡቲ ካዘጋጀው 2ኛው የኢትዮ ጂቡቲ ቢዝነስ ማስፋፍያ ጉባኤ ጎን ለጎን የተካሄደ ነው።






የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ሰብስብ አባፊራ አባጆቢር የአሳላ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በአሰላ ከተማ ለሚገኙ ነጋዴዎች እና አምራቾች ፋይናንስ በማቅረብና የተሻለ አገልግሎት አሰጣጥን ተግባራዊ በማድረግ ላደረገው አስተዋጽኦ እውቅና መስጠቱ እጅግ የሚበረታታና የሚያስመሰግን ተግባር መሆኑን ገለጹ።





ፕሬዝዳንቱ በመልዕክታቸው ለምክር ቤቱ ፕሬዚዳንት አቶ አድማሱ ድሪባም ምስጋናቸውን አቅርበዋል።





**የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት እና  የአለም ባንክ የግሉ ዘርፍን  ተወዳዳሪነት ሊያጎለብቱ በሚችሉ የአቅም ግንባታ ተግባራት ዙሪያ በጋር ለመስራት በሚያስችሉ ጉዳዮች ላይ ተወያዩ፡፡**

የም/ቤቱ ዋና ፀሐፊ ዶ/ር ቀነኒሳ ለሚ (ተባባሪ ፕሮፌሰር) እና  በአለም ባንክ የግሉ ዘርፍ ልማት ከፍተኛ ባለሙያ አቶ ብስራት ተሾመ የግሉ ዘርፍ በአገር ኢኮኖሚ ዕድገት ውስጥ መጫወት የሚገባውን ሚና ለማጎልበት በሚያስችሉ የአቅም ግንባታዎች ላይ በጋራ ለመስራት በሚያስችሉ ጉዳዮች ላይ በሰፊው ተወያይተዋል፡፡





የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት  የአገሪቱ የግሉ ዘርፍ በአህጉራዊና አለም-አቀፋዊ ውድድር ውስጥ ብረቱ ተፎካካሪ ለመሆን ብቻ ሳይሆን ተፎካክሮም ተገቢውን የገበያ ድርሻ እንዲይዝ ከማድረግ አኳያ ከተለያዩ የልማት አጋሮች ጋር እየሰራ መሆኑን ዋና ፀሐፊው ዶ/ር ቀነኒሳ አስረድተዋል፡፡

የተለያዩ የልማት ፕሮጀክቶችን በፋይናንስ በመደገፍ ከሚታወቀው የአለም ባንክ ጋርም በግሉ ዘርፍ አቅም ግንባታ ላይ ለመስራት ፍላጎት አንዳለው ገልፀዋል፡፡

በአለም ባንክ የግሉ ዘርፍ ልማት ከፍተኛ ባለሙያ አቶ ብስራት ተሾመ በበኩላቸው በተለይም የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች አሁን በተጀመረው የካፒታል ገበያ ወስጥ የሚፈጠረውን ዕድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ እና የሚያገኙትን ካፒታል በአግባቡ መጠቀም የሚያስችል አቅም እንዲኖራቸው በስልጠና ማገዝና ለተወዳዳሪነት ብቁ ማድረግ ላይ የአለም ባንክ ከኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ጋር ለመስራት ፍላጎት እንዳለው ገልፀዋል፡፡



**የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት እና CIPE EHIOPIA (Center for International Private Enterprise)  የተሰኘ አለም አቀፍ የግል ዘርፍ ኢንተርፕራይዝ ማዕከል  የግሉ ዘርፍ በአገሪቱ የኢኮኖሚና የሰላም ግንባታ ውስጥ ሊኖረው በሚገባ ሚና ዙርያ በጋራ ለመስራት ተወያዩ፡፡**



በኢትዮጵያ የግሉ ዘርፍ በአገር ኢኮኖሚ እና  ሰላም ግንባታ ውስጥ ተገቢውን ሚና እንዲጫወት ተገቢው ትኩረት ተሰጥቶት አስፈላጊውን ድጋፍ ለማድረግ የግሉ ዘርፍ ድምፅ የሆነው የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤትና  በአለም አቀፍ ደረጃ የዲሞክራሲ ስርአት እንዲጎለብትና ገበያ ተኮር ማሻሻያዎች እንዲደረጉና የግሉ ዘርፍ ሚና እንዲጎላ ለማድረግ የሚሰራው በኢትዮጵያ አለም አቀፍ የግል ዘርፍ ኢንተርፕራይዝ (CIPE) አብሮ ለመስራት ምክክር አድርገዋል፡፡

የምክር ቤቱ ዋና ፀሐፊ ዶ/ር ቀነኒሳ ለሚ (ተባባሪ ፕሮፌሰር) እና የCIPE ETHIOPIA ዳይሬክተር አቶ ኃይለመለኮት አስፋው የአገሪቱን የኢኮኖሚ ዕድገት ለማፋጠን የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ መጎልበት እንዳለበት በውይይታቸው ያነሱ ሲሆን ለዚህ ዋነኛ መሰረት በሆነው የሰላም ጉዳይ ላይ በጋራ እንደሚሰሩና አስፈላጊውን ድጋፍ እንደሚያደርጉም አቶ ኃይለመለኮት አሳውቀዋል፡፡



ከዚህም በተጨማሪ የ2030 ዲጂታል ኢትዮጵያ ፕሮግራምን እውን ለማድረግ የሚረዳውን ዲጂታል ኢኮኖሚ ተግባራዊ ለማድረግ በሚደረገው ጥረት ውስጥ የግሉን ዘርፍ አቅም ለማጎልበትም አብሮ ለመስራት ሁለቱ ተቋማት ተስማምተዋል፡፡



**የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ዋና ጸሐፊ ዶክተር ቀነኒሳ ለሚ (ተባባሪ ፕሮፌሰር) በኢትዮጵያ የማሌዥያ ኤምባሲ ልዑክ ጋር ተወያዩ፡፡**





በውይይታቸውም የሁለቱን ሀገራት የቢዝነስ ትስስር ማሳደግ በሚቻልባቸው ጉዳዮች ዙሪያ ተነጋግረዋል፡፡

ዶክተር ቀነኒሳ በኢትዮጵያ ስላለው የንግድና ኢንቨስትመንት ምቹ ሁኔታ ያብራሩ ሲሆን በሀገራዊ የኢኮኖሚ ሪፎርም ትኩረት ስለተሰጣቸው የኢንቨስትመንት መስኮች ገልጸውላቸዋል፡፡

በኢትዮጵያ የማሌዥያ ቋሚ ጉዳይ አስፈጻሚ (chargé d'affaires) ሞህድ አፋንዲ አቡ በክር በበኩላቸው ማሌዥያ ከኢትዮጵያ ጋር ያላትን የኢኮኖሚ ትስስር ለማሳደግ ፍላጎት እንዳላት ገልጸዋል፡፡



ከምክር ቤቱ ጋር በመተባበር በቀጣይ ህዳር ወር የኢትዮ-ማሌዥያ ቢዝነስ ፎረም በአዲስ አበባ እንደሚካሄድም በውይይቱ ወቅት ተጠቁሟል፡፡

ባለፈው ዓመት ጥቅምት ወር የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት ዶክተር ዓይናለም አባይነህ ከማሌዥያ ብሔራዊ የንግድና ኢንዱስትሪ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ዳቶ ሰሪ ጎባላክሪሽናን ጋር የመግባቢያ ስምምነት መፈራረማቸው የሚታወስ ነው፡፡



Dr. Kenenisa Lamie (Associate Professor), Secretary General of the Ethiopian Chamber of Commerce and sectoral associations (ECCSA), met with a delegation from the Malaysian Embassy in Ethiopia.

During their meeting, they discussed issues that could enhance business ties between the two countries.

Dr. Kenenisa explained the favorable trade and investment environment in Ethiopia and highlighted the investment areas that have been given priority in the national economic reform.

The Malaysian Chargé d'affaires in Ethiopia, Mohd Afandi Abu Bakar, for his part, expressed Malaysia's interest in increasing its economic ties with Ethiopia.

It was also noted during the discussion that the Ethiopia-Malaysia Business Forum will be held in Addis Ababa in the coming November in collaboration with ECCSA.

It is worth noting that in October last year, Dr. Aynalem Abayneh, Vice President of the Ethiopian Chamber of Commerce and sectoral associations, signed a Memorandum of Understanding (MoU) with Dato' Seri Gobalakrishnan, President of the Malaysian National Chamber of Commerce and Industry.

## የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት በተለያዩ የቢዝነስ ዘርፎች ለተሠማሩ ሴቶች ሥልጠና እየሠጠ ነው።





ሥልጠናውም በማርኬቲንግ እና በቢዝነስ ሊደርሺፕ ላይ ያተኮረ ነው።

በሥልጠናው ማሥጀመሪያ ላይ የምክር ቤቱ ዋና ጸሐፊ ዶክተር ቀነኒሳ ለሚ (ተባባሪ ፕሮፌሠር) የኢኮኖሚው ዋና አንቀሣቃሽ የሆኑት ሴቶች አቅማቸው እንዲጎለብትና ውጤታማ ቢዝነስ መሥራት እንዲችሉ ምክር ቤቱ ትኩረት ሠጥቶ እየሠራ ሥለመሆኑ ገልጸዋል።

ሰልጣኞችም ሥልጠናውን በአግባቡ በመከታተል የሚያገኙትን እውቀት ተግባራዊ በማድረግ ዘመናዊና ጊዜው የዋጀ ቢዝነስ መምራት እንደሚገባቸውም አሥገንዝበዋል።





ሰልጣኞችም በቆዳና የቆዳ ውጤቶች፣ በቡና፣ አልባሣት፣ በባልትና እንዲሁም በሌሎች የቢዝነስ ዘርፎች የተሠማሩ ናቸው።

## ሴቶች በሥልጠና ያገኙትን እውቀት ተግባራዊ በማድረግ ተወዳዳሪ መሆን እንዳለባቸው ተገለጸ።





የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ከተለያዩ ዘርፎች ለተውጣጡ ሴቶች ሲሰጠው የነበረው ሥልጠና ተጠናቋል።

ሴት የቢዝነስ ባለቤቶች በማርኬቲንግ እና በሥራ አመራር ዙሪያ ነበር ሥልጠናውን ሲከታተሉ የቆዩት።

የሥልጠናው ተሣታፊዎችም በቡና፣ በቆዳ እና ቆዳ ውጤቶች ፣ በአልባሣት፣ በባልትና እንዲሁም በሌሎች ዘርፎች ላይ የተሠማሩ ናቸው።

በማጠቃለያ ፕሮግራሙ ላይ የተገኙት የምክር ቤቱ የአባላት ድጋፍ ዳይሬክተር አቶ እሱባለው ተስፋ ሠልጣኞች ያገኙትን እውቀት ወደ ተግባር በመቀየር ዘመናዊ አሠራርን በመተግበር ተወዳደሪ እንዲሆኑ በማሥገንዘብ ምክር ቤቱም በተለያዩ ዘርፎች ሴት የቢዝነስ ባለቤቶችን እንደሚደግፍ አንሥተዋል።



ሰልጣኞቹም ከሥልጠናው የተሻለ ግንዛቤ ማግኘታቸውን ጠቁመው ምክር ቤቱ አቅማቸውን ለመገንባት ሥልጠናውን በማዘጋጀቱ ምሥጋናቸውን አቅርበዋል።

ሌሎች ሥልጠናውን ያላገኙ አካላትም የምክር ቤቱን የሥልጠና እድሎች እንዲጠቀሙና የራሣቸውንም ሆነ የሠራተኞቻቸውን እውቀትና ክህሎት እንዲያሣድጉ ሠልጣኞቹ መልዕክታቸውን አሥተላልፈዋል።

## ለማዕከላዊ ኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤቶች አመራሮች በአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጠና መሠረታዊ መርሆች ላይ የግንዛቤ መፍጠርያ ስልጠና በሆሳዕና ከተማ እየተሰጠ ነዉ።






ስልጠናዉ የተዘጋጀዉ በኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት መክር ቤትና በGIZ Programme Support to Afrca ትብብር ሲሆን ስልጠናዉን በንግግር የከፈቱት የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ዋና ፀሐፊ ዶ/ር ቀነኒሳ ለሚ(ተባባሪ ፕሮፌሰር) የአገራችን የግሉ ዘርፍ እየገባበት ላለዉ አህጉራዊና አለምአቀፋዊ ብርቱ ፉክክሮች ከወዲሁ እራሱን ማዘጋጀት አለበት ብለዋል።




የአገር ኢኮኖሚ እንዲያድግ የግሉ ዘርፍ መጠናከር አለበት ያሉት ዋና ፀሐፊዉ ለግሉ ዘርፍ መጠናከር ደግሞ በየደረጃዉ ያሉት የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤቶች መጠናከር እንዳለባቸዉ አሳስበዋል።

የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት አቶ ሳኒ ሀሰን በበኩላቸዉ የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የክልሉ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤቶች አመራሮች በወቅታዊዉና ወሳኙ የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጠና ዙርያ ተገቢዉን ግንዛቤ አግኝተዉ በዚህ ልክ አባሎቻቸዉን የማስገንዘብና የማዘጋጀት ስራ እንዲሰሩ ስልጠናዉን በማመቻቸቱ አመስግነዋል።

የግንዛቤ መፍጠርያ ስልጠናዉን የሰጡት በGIZ AU የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጠና የኢኮኖሚ አማካሪ የሆኑ አቶ ዉብእሸት ካሳ ሲሆኑ የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጠና መሠረተ ሀሳቦች: ዋና ዋና ምሰሶዎች: ሊያጋጥሙ የሚችሉ ተግዳሮቶችና መፍትሔዎቻቸዉ በስልጠናዉ ተዳሰዋል።





የማዕከላዊ ኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የቦርድ አመራሮችና በየደረጃዉ ካሉ የክልሉ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤቶች የተዉጣጡ አመራሮች በስልጠናዉ እየተሳተፉ ነዉ።

## የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት በተለያዩ የቢዝነስ መሥኮች ሥልጠና ለሚሠጡ አሠልጣኞች ሥልጠና እየሠጠ ነው።





ከSNV - LIWAY ፕሮጀክት ጋር በመተባበር የተዘጋጀው የአሰልጣኞች ሥልጠና የቢዝነስ ተቋማትን አቅም ለመገንባት ያለመ ነው።

አሠልጣኞቹም በዲጂታል ማርኬቲንግ፣ በማሥተዋወቅ እና ብራንዲንግ እንዲሁም በማህበራዊ ሚዲያ ማርኬቲንግ እና በሌሎችም መሥኮች ሥልጠናዎችን የሚሠጡ ናቸው።

የምክር ቤቱ ምክትል ዋና ጸሐፊ አቶ ጳደቀ ድጋፌ በሥልጠናው ማስጀመሪያ ላይ እንደገለጹት የአባላትንና የቢዝነስ ተቋማትን አቅም እንዲያድግ እንዲሁም የአፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጣና ሥምምነት ትግበራ፣ የአለም ንግድ ድርጅት አባልነትን ታሣቢ ያደረገ ቢዝነስ እንዲኖር በማለም የተዘጋጀ ሲሆን ቀጣይነት ያለው ነው።





ሥልጠናውን በአጋርነት ያዘጋጀው SNV የተሠኘው ዓለም አቀፍ ተቋምም በኢትዮጵያ በተለያዩ ዘርፎች በርካታ ፕሮጀክቶች ላይ እየሠራ ያለ ተቋም ነው።

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ከሚሠጣቸው አገልግሎቶች አንዱ ለንግዱ ማኅበረሰብ የአቅም ግንባታ ስልጠና መሥጠት መሆኑ ይታወቃል።










# የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት







# የግሉ ዘርፍ ድምጽ!



የንግድ ምክርቤቱ ራዕይ ፣ተልዕኮ ፣ እሴቶች እና ቀዳሚ ስትራቴጂካዊ አምዶች

## ራዕይ

“በግሉ ዘርፍ የሚመራ ኢኮኖሚና አካታች ዕድገት በሁለት የስትራቴጂክ ዘመናት ውስጥ እውን ሆኖ ማየት”

## ተልዕኮ

“የኢትዮጵያን የግል ዘርፍ በመወከል፣ በመደገፍና ለመብትና ጥቅሙ አድቮኬት በማድረግ፤ ንግድን፣ ኢንቨስትመንትንና ፈጠራን በማስተዋወቅና በማበረታታት አካታች ኢኮኖሚያዊ ዕድገትና ብልፅግናን ማምጣት”

## ዕሴቶች

- ታማኝነት
- ሙያዊ ብቃት
- አባላት ተኮር ምላሽ ሰጪነት
- ትብብራዊ ጥምረት
- ግልፅነት
- ተጠያቂነት
- ማህበራዊ ኃላፊነት

## ቀዳሚ ስትራቴጂካዊ ጉዳዮች (ስትራቴጂካዊ አምዶች)

1. አድቮኬሲና የፖሊሲ ተፅዕኖ
2. ጠንካራ የአባላት ተሳትፎና ድጋፍ
3. የሀብት ማሰባሰብና በአግባቡ መጠቀም
4. የአቅም ግንባታና ሥርዓት ማሻሻያ
5. ቴክኖሎጂን ማካትት እና ዲጂታል ሽግግር
6. ዘላቂነት ያለው ማኅበራዊ ኃላፊነት
7. ንግድና ኢንቨስትመንት ማስፋፋት
8. ሁሉን-አቀፍ ጉዳዮች (Cross-cutting issues)

**ዋና አዘጋጅ:-**

**ተሾመ ዋቅጂራ**

**ም/ዋና አዘጋጅ:-**

**ደበበ አበበ**

**አዘጋጅ**

**ስማቸው ተበጀ**

**ፎቶግራፍ**

**ያለምፍሬ በቀለ**




**The Ethiopian Chamber of Commerce and Secoral Associations (ECCSA)**

ስልክ: +251115514005

ፋክስ: + 251115517699

P. O. Box 517,

ኢ-ሜይል: info@ethiopianchamber.com

ድረ ገጽ: www.ethiopianchamber.com

ቴሌግራም t.me/ethiopiachamber

ትዊተር https://twitter.com/EthiopiaChamber

ፌስ ቡክ: https://www.facebook.com/EthiopianChamber

Youtube: https://www.youtube.com/channel/UCMEZ4TO8dQiIJvk2IQkTxhA

Linkedin(ሊንክዲን):https://www.linkedin.com/company/ethiopianchamber/in